## ስለ ፡ "የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ መግቢያ" ፡ የተሰጠ ፡ ተጨማሪ ፡ ማብራሪያ ።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ ታትሞ ፡ በወጣው ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ "የኢትዮጵያ ፡ የሕግ፡ ምንጮች ፡ መግቢያ" ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ በጻፍሁት ፡ አጭር ፡ ድርሰቴ ፡[1] ከኔ ፡ የበለጠ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ የተዘነጋውን ፡ ክፍል፡ በይበልጥ ፡ ለማዳበር ፡ ይህንን ፡ የመጀመሪያ ፡ ድርሰት ፡ በማንበብ ፡ እንዲነሳሱ ፡ ምኞቴን ፡ ገልጬ ፡ ነበር ። ስለ ፡ ሕግ ፡ ሳይንስና ፡ በተለይም ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ ብዙ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ክሽችኖቪች ፡ በዚህ ፡ መጽሔት ፡ እትም ፡ ውስጥ ፡ ይህንኑ ፡ ምኞቴን ፡ ፈጽመዋል ።[2]

ከሰጡትም ፡ ሐተታ ፡ መሃከል ፡ አንዳንዶቹ ፡ ስለ ፡ ሰፊው ፡ የወል ፡ ሕግ ፡ (ጁሪስፕሩደንስ) ፡ ክፍል ፤ (ይህ ፡ ክፍል ፡ በታወቁ ፡ ምክንያቶች ፡ በድርሰቴ ፡ ውስጥ ፡ ሳይጠቃለል ፡ ቀርቷል) ፥ አንዳንዶቹ ፡ በድርሰቴ ፡ ውስጥ ፡ በተለይ ፡ ስለ ፡ ተጠቀሰው ፡ ክፍል ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ የተባለው ፡ አጭር ፡ ድርሰት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ መስፋፋት ፡ ላይ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ታላላቅ ፡ ውጤቶች ፡ ያወሳሉ ። የፕሮፌሰር ፡ ክሽችኖቪችን ፡ ትችት ፡ ካነበብኩ ፡ በኋላ ፡ ምናልባት ፡ ለአንባብያን ፡ ሰውር ፡ ሁነው ፡ ሊቀሩ ፡ ስለሚችሉት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጭብጦች ፡ ጥቂቶቹን ፡ ለማብራራት ፡ አንዳንድ ፡ ማብራሪያ ፡ ሐሳቦችን ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ አግኝቸዋለሁ ።

## የ"ሕግ" ፡ ፍችና ፡ የ"ሕግ ፡ ምንጮች" ።

የሥራ ፡ ጓደኛዬ ፡ ስለ ፡ "ሕግ" ፡ ፍችና ፡ ስለ ፡ "ሕግ ፡ ምንጮች ፡ ያቀረቡኩትን ፡ ሐተታ ፡ "ሰፊ ፡ አከራካሪና ፡ በከፊልም ፡ ዋጋቢስ" ፡ ነው ፥ ብለዋል ። የኔ ፡ ዓላማ ፡[3] የእርሳቸውን ፡ መስመር ፡ ለመከተል ፡ ሳይሆን ፥ በሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ዘንድ ፡ ያሉትን ፡ የአስተያየቶች ፡ ልዩነት ፡ ለመግለጽ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ሕግ ፡ የሚገኘው ፡ "ከድርጊቶችና ፡ ኢንስቲቱሲዮኖች" ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ "ከደንቦች" ፡ ነው ፡ በሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ላይ ፥ በርከት ፡ ያሉ ፡ የአውሮፓና ፡ የእንግሎ ፡ ሳክሶን ፡ ደራሲዎች ፡ ሕግ ፡ ከደንቦች ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የተመሠረተው ፡ የሚለው ፡ ፍች ፡ በቂ ፡ አለመሆኑን ፡ በቅርብ ፡ ዓመታት ፡ ተከራክረውበታል ።[4] እንደዚሁም ፡ የዚህ ፡ ድርሰት ፡ ጸሐፊ ፡ በሰጠው ፡ ፍች ፡ ላይ ፡ የሕግ ፡ ዓላማ ፡ መጠቀሱ ፡

1. የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፥ ቦልዩም ፡ ፫ (፲፱፻፶፰) ገጽ ፥ ፪፻፳፮ ፡ (ከዚህ ፡ በኋላ ፡ "መግቢያ" ተብሎ ፡ ይጠራል) ።
2. የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፥ ቦልዩም ፥ ፫ (፲፱፻፶፰) ገጽ ፡ ፭፻፴(ከዚህ ፡ በኋላ ፡ "ትችት" ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል) ።
3. ትችት ፥ ገጽ ፡ ፭፻፱ ።
4. ለምሳሌ ፡ ክኤች ፡ ቤከርት ፡ የተጻፈውን ፡ ኢንትሮዳክሽን ፡ አ ፡ ሌቀዶ ፡ ደ ፡ ድሮ ፡ (ብሩክ ፡ ቤልስ ፡ ፲፱፻፳፱ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) ፥ ገጽ ፡ ፻፴፯—፵፩ ፥ ፻፶፱—፷፭ ፥ እና ፡ ፫፻፲—፴፫ ፡ ይመለከቷል ። ስለ ፡ ኤውሮፓ ፡ የሕግ ፡ አስተሳሰብ ፡ በውስጡ ፡ በብዛት ፡ ተጠቅሶ ፡ ይገኛል ። በተጨማሪም ፡ ክኤም ፡ ቪሌይ ፡ የተጻፈውን ፡ ሁን ፡ ደፊኒሲዮን ፡ ዱ ፡ ድሮ ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ሥር ፡ በአርካይቭስ ፡ ዱ ፡ ፊሎዞፊ ፡ ዱ ፡ ድሩዋ ፡ ኤ ፡ ሂስቷር ፡ (ፓሪስ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ እ ፡ አ ፡) ገጽ ፡ ፵፰ ፡ ተመልከት ። ስለሌላውንና ፡ ስለ ፡ አሜሪካውያን ፡ ሪያሊስት ፡ ጽንሰ ፡ ሐሣብ ፡ አጭርና ፡ የተብራራ ፡ መቅድም ፡ በሲ ፡ ኬ ፡ አለን ፡ በተጻፈው ፤ ሎው ፡ ኢን ፡ ዘ ፡ ሜኪንግ ፡ (ኦክስፎርድ ፡ ፲፱፻፳፯) ፡ ገጽ ፡ ፵፩—፵፰ ፡ ሊገኝ ፡ ይቻላል ።

በአንዳንዶቹ ፡ አግባብ ፡ እንደሌለው ፡ ሲቆጠር ፡ በሌሎች ፡ ግን ፡ ለፍችው ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ።[5] እነዚህ ፡ ደራሲዎች ፡ ስለመስፋፋት ፡ ዓላማ ፡ በተለይ ፡ ሲጠቅሱ ፡ ቃሉን ፡ የተጠቀሙበት ፡ የእድገትን ፡ ስሜት ፡ በሰፊው ፡ ለማሳየት ፡ እንጂ ፡ በልማት ፡ ወደኋላ ፡ ቀርተዋል ፡ ተብለው ፡ ስለሚነገሩት ፡ አገሮች ፡ በሚነገርበት ፡ ጊዜ ፡ ለእድገት ፡ የተሰጠውን ፡ ጠበብ ፡ ያለውን ፡ ስሜት ፡ በመውሰድ ፡ አይደለም ። ሰፊውን ፡ ፍች ፡ ይዘን ፡ ስለኅብረተ ፡ ሰብ ፡ በምንናገርበት ፡ ጊዜ ፡ ቃሉ ፡ የተለየ ፡ ግላዊ ፡ (ሰብጀክቲቭ) ፡ ትርጉም ፡ እንሳዳለውና ፡ አንድ፡ የተወሰነ ፡ ኅብረተ ፡ ሰብን ፡ ለማዳበር ፡ ስለሚቻልበት ፡ ዘዴ ፡ በጣም ፡ የተለያዩ ፡ አስተያየቶች ፡ እንዳሉ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በመጨረሻም ፡ የሥራ ፡ ጓደኛዬ ፡ እንደሚሉት ፡ ከመንግሥት ፡ በቀር ፡ ሌሎች ፡ በሕዝብ ፡ የታወቁ ፡ ድርጅቶች ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ሕግ ፡ ለመፍጠር ፡ ወይም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ አይችሉም ። በቀድሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አልነበረም ። ለምሳሌ ፡ በአሥራ ፡ አራተኛው ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ስነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሁኔታ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶችን ፡ ብቻ ፡ የሚያጠቃልል ፡ ፍች ፡ ይስማማዋል ፡ ብንል ፡ ያለጥርጥር ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ የሆኑ ፡ ድርጊቶችና ፡ ድርጅቶችን ፡ (ኢንስቲቱሲዮኖችን) ፡ ከሕግ ፡ ክፍል ፡ በርግጥ ፡ መሠረዝ ፡ ይሆንብናል ።[6]

እሁን ፡ ወደ ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡ ትርጉም ፡ እንመለስ ። በሥፍራ ፡ ጥበት ፡ ምክንያት ፡ ሳልጠቅሳቸው ፡ የቀረሁትን ፡ "ሕጋዊና""ሕጋዊ ፡ ያልሆነ" ፡ ለሚሉት ፡ ቃላት ፡ ትክክለኛውን ፡ ትርጉም ፡ ለመስጠት ፡ ከድርሰታቸው ፡ ጥቂቱን ፡ ክፍል ፡ በመሰዋታቸው ፡ የሥራ ፡ ጓደኛዬን ፡ ሳላመሰግናቸው ፡ አላልፍም ። ነገር ፡ ግን ፡ በድርሰቱ ፡ ውስጥ ፡ በተሰ ጉት ፡ ምሳሌዎች ፡ "ሕጋዊ" ፡ ማለት ፡ "ሕግን ፡ የሚያፈልቅ ፡ "ሕጋዊ ፡ ያልሆነ" ፡ ማለት ፡ ደግሞ ፡ የሕግ ፡ ማስረጃ ፡ እንደሆነ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ። "በሥርዓትና ፡ በደንብ ፡ የተገኙ ፡ የሕግ፡ ምንጮች"፡[7] በአዋጅ ፡ የወ ጉ ፡ ሕጎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ የሚለው ፡ ሃሳብ ፡ አንዳንዶቹ ፡ የሚደግፉትና ፡ ሌሎች ፡ ግን ፡ በጥብቅ ፡ የሚቃወሙት ፡ አስተያየት ፡ ነው ።[8] የሥራ ፡ ጓደኛዬ ፡ ስለ ፡ ልማድ ፡ ሕግ ፡ ፍች ፡ ያደረጉት ፡ ሐታተም ፡ እንዲሁ ፡ ደጋፊዎችም ፡ ተቃዋሚዎችም ፡ ያሉት ፡ አስተያየት ፡ ነው ።[9]

---

5. የሕግ ፡ ተግባር ፡ ስሕግ ፡ ፍች ፡ ከሚያስፈልጉት ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ስለመሆኑ ፡ ከላይ ፡ ባ፭ኛው ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ እንደ ፡ ተጠቀሰው ፡ የአለን ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፳፯ ፡ ከ፫ ፡ ደብልዩ ፡ ፔተን ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ቴክስት ፡ ቡክ ፡ ኦፍ ፡ ጁሪስፕሩደንስ ፡ (ኦክስፎርድ ፡ ፲፱፻፵፱) ፡ ገጽ ፡ ፳፮ ፡ የመሰሉ ፡ የመማሪያ ፡ መጻሕፍትን ፡ ይመለከቷል ።
6. ይህ ፡ በመግቢያው ፡ በገጽ ፡ ፻፺፯ ፡ ተጠቅሷል ። ስለ ፡ ማንጸጸርያ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ታሪካዊ ፡ ዘዴዎች ፡ (ቴክኒክስ) ፡ በሚታሰብበት ፡ ጊዜ ፡ ምንግ ፡ ሰው ፡ ጠባቡን ፡ ስሜት ፡ የሚያመለክቱትን ፡ ስያሜዎች ፡ መከተል ፡ የለበትም ።
7. ትችት ፡ ገጽ ፡ ፯፻፲፮ ፡ ይመለከቷል ።
8. ከላይ ፡ ባ፭ኛው ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የቢከርትን ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፻፭፱—፻፷፩ ፡ እና ፡ ስለ ፡ ኮንቲኔንታል ፡ የሕግ ፡ አስተሳሰብ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ጥቅሶች ፡ በተጨማሪ ፡ ይመለከቷል ። በነዚህ ፡ ገጾች ፡ ያሉት ፡ ሐሣቦች ፡ በፕሮፌሰር ፡ ቢከርት ፡ መጽሐፍ ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ተስፋፍተው ፡ ይገኛሉ ።
9. ደህና ፡ ደረጃ ፡ ያላቸው ፡ የመማሪያ ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ ከጥቂቶቹ ፡ በቀር ፡ ልማድ ፡ የሕግ ፡ ምንጭ ፡ እንደሆነ ፡ ይናገራሉ ። በሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ "ልማዳዊ ፡ ሕግ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከሀገር ፡ ተወላጆች ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ የተሳሰረ ፡ ስሜት ፡ አለው ። ይህም ፡ ስያሜ ፡ ቅኝ ፡ ገዥ ፡ የሆኑ ፡ ኃያላን ፡ መንግሥታት ፡ እንዲሠራበት ፡ የፈቀዱትን ፡ የአፍሪቃን ፡ የአሜሪካን ፡ ወይም ፡ የእስያን ፡ ሕግ ፡ ያመለክቷል ። ይህ ፡ ግን ፡ የባሰ ፡ ስህተት ፡ ነው ። ቅኝ ፡ ሀገር ፡ ስለነበሩት ፡ ሀገሮች ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የተደረገው ፡ ጥናት ፡ ስለልማድ ፡ እንደማወቃቸው ፡ መጠን ፡ በአጋጊ ፡ ስለወጣ ፡ ሕግ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ስለሚገኝ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ስለሕጋዊ ፡ ሲያንስ ፡ እንደሚያውቁ ፡ በግልጽ ፡ ያስረዳል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ፍች ፡ እስካሁን ፡ የተደረገው ፡ ሐተታ ፡ ከልክ ፡ በላይ ፡ ነው ። ብቻ ፡ የድርሰቱ ፡ ዓላማ ፡ ካምስት ፡ እና ፡ ከስድስት ፡ መቶ ፡ ዘመናት ፡ በፊት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡ ምን ፡ ምን ፡ እንደነበሩ ፡ ለተራው ፡ አንባቢ ፡ ባጭሩ ፡ ለመግለጽ ፡ እንደነበረ ፡ ደግሜ ፡ እንዳስታውስ ፡ እፈቅዳለሁ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ያለፉትን ፡ ሃምሳ ፡ ዓመታት ፡ የፖለቲካና ፡ የሕግ ፡ ፅንስ ፡ ሐሣቦችን ፡ በሁሉም ፡ ረገድ ፡ ባያመለክቱም ፡ [10] በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ለነበረው ፡ ሁኔታ ፡ ተስማሚ ፡ ፍችዎች ፡ መገኘት ፡ ይገባቸዋል ።

## የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ።

ወደ ፡ ሰዓት ፡ ሠሪዎች ፡ ጣጣ ፡ ከመመለሳችንና ፡ ሰዓቶች ፡ በትክክል ፡ እንዲሠሩ ፡ ለማስተካከል ፡ ከመሞከራችን ፡ በፊት ፡ እስቲ ፡ መጀመሪያ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ እናስብ ። ሐተታ ፡ የሚያስፈልገው ፡ የመጀመሪያው ፡ ሐሣብ ፡ ልማድ ፡ ለአዲሲቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስላለው ፡ አግባብ ፡ ነው ። በ"መግቢያው" ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ሁሉ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ክሸችኖቪች ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ለጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ሲያጠኑ ፡ ቆይተዋል ። [11] በ"መግቢያው" ፡ ውስጥ ፡ ከፕሮፌሰር ፡ ክሸችኖቪች ፡ አስተያየት ፡ ጋራ ፡ የማልስማማባቸውን ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶችን ፡ ጠቅሼ ፡ ነበር ። አንደኛ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ክሸችኖቪች ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በጻፉት ፡ በዋናው ፡ ድርሰታቸው ፡ የዘረዘሩዋቸው ፡ የልማድ ፡ አገልግሎቶች ፡ የልማድ ፡ ክልል ፡ ጠባብና ፡ በጣም ፡ የተወሰነ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ የሚያበቁ ፡ አልመሰለኝም ። [12] እርግጥ ፡ ነው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ "በጣም" ፡ ስለመሰሉት ፡ ቃላት ፡ ትርጉም ፡ ለመከራከር ፡ ይችላል ። ቢሆንም ፡ በፊት ፡ የገለጽኩትን ፡ አስተያየቴን ፡ አሁንም ፡ አልለውጥም ። ሁለተኛ ፡ ጊዜአዊ ፡ ተብለው ፡ የወጡና ፡ አሁንም ፡ የጸኑ ፡ አንዳንድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥሮች ፡ (ቁጥር ፡ ፫ሺ፫፻፴፫ እና ፡ ፫ሺ፫፻፶፩) ፡ የሥራ ፡ ጓደኛዬ ፡ በጻፉት ፡ ድርሰት ፡ ውስጥ ፡ ሳይጠቀሱ ፡ ተዘልለዋል ። እንዚህም ፡ "ለጊዜው" ልማድ ፡ እንዲሠራበት ፡ አይፈቅድም ፤ ብሎ ፡ ለመቃወም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። እንደ ፡ እውነቱም ፡ ከሆነ ፡ የሥራ ፡ ጓደኛዬም ፡ እንዲሁ ፡ ብለው ፡ አልተቃወሙኝም ። ነገር ፡ ግን ፡ ለነዚህ ፡ አንቀጾች ፡ በእኔ ፡ የተሰጣቸው ፡ ትርጉም ፡ በስሕተት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ፡ ብለዋል ። በጣም ፡ ረቂቅ ፡ የሆነውን ፡ ሐተታቸውን ፡ (የሐተታው ፡ አጻጻፍ ፡ ለተራው ፡ ሕዝብ ፡ ተብሎ ፡ ስለተጻፈው ፡ ድርሰት ፡ እንደማያገለግል ፡ ግልጽ ፡ ነው) በጥንቃቄ ፡ ደጋግሜ ፡ ካነበብኩ ፡ በኋላ ፡ በእኔ ፡ ድርሰት ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሰውን ፡ በትችታቸው ፡ የተደገፈው ፡ ነገር ፡ በፍጹም ፡ አንድ ፡ እንደሆነ ፡ ተሰማኝ ።

ሐተታ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሁለተኛው ፡ ነገር ፡ ጋብቻ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ክሸችኖቪች ፡ እንደሚሉት ፡ ድርጅት ፡ (ኢንስቲቱስዩን) ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ እኔ ፡ እንደምለው ፡ ውል ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ነው ። ድርጅት ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ በመደገፍ ፡ የሚቀርበው ፡ ክርክር ፡ ስምምነቱ ፡ ንብረትን ፡ የማይመለከትና ፡ በአስገዳጅ ፡ ሕጐች ፡ የሚገዛ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ነው ። [13] ይህንን ፡ የሚቃወሙ ፡ ክርክሮች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

---

10. በ፮ኛው ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ላይ ፡ የተሰጠውን ፡ አስተያየት ፡ ይመለከቷል ።
11. በ፪ኛው ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ላይ ፡ በተጻፈው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ባ፲፮ኛው ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ድርሰቶች ፡ ተመልከት ።
12. "በመግቢያው" ፡ ውስጥ ፡ በእስገራሚ ፡ ትንተና ፡ የተጻፈውን ፡ ሐተታ ፡ በገጽ ፡ ፪፻፲—፪፻፲፩ ፡ እና ፡ በትችቱ ፡ ላይ ፡ በገጽ ፡ ፪፻፲ ፡ ተመልከት ።
13. በትችቱ ፡ ውስጥ ፡ በገጽ ፡ ፪፻፲፩ ፡ ተመልከት ።

በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የንብረት ፡ ሐሣብ ፡ የሌለ ባቸው ፡ ግን ፡ ድርጅቶችን ፡ (ኢንስቲቱሽኖችን) ፡ የማይመሠርቱ ፡ ስምምነቶች ፡ ይገኛሉ ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ቦታ ፡ ለመኖር ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ተወሰነ ፡ ቦታ ፡ ለመሄድ ፤ (አድራጎቱ ፡ በሕጋዊ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ተመ ሠረተበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ) (ያንኑ ፡ መሠረታዊ ፡ ወሰን ፡ ሳያልፍ) ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ተቀጥሮ ፡ ለመሥራት ፡ ወይም ፡ ላለመሥራት ። ወይም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሰውነ ቱን ፡ እንዳሻው ፡ ለማድረግ ፡ ስምምነት ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ። በነዚህ ፡ በተጠቀ ሱት ፡ ሁሉ ፡ የድርጊቱ ፡ ዓላማ ፡ የገንዘብን ፡ ነገር ፡ ላይመለከት ፡ ይችላል ፤ ብዙው ንም ፡ ጊዜ ፡ አይመለከትም ።[14] እንግዲህ ፡ እነዚህ ፡ ስምምነቶች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ቀዋሚ ፡ ደንብ ፡ ይመሠርታሉ ፡ ብለን ፡ ለመደምደም ፡ እንችላለንን ? እንዲሁ ፡ ለማለት ፡ መቻላችን ፡ በጣም ፡ ያጠራጥራል ።

በተጨማሪም ፡ ስለጋብቻ ፡ የሚናገሩ ፡ ቁጥሮች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። እነሱም ፡ እንኳንስ ፡ አስገዳጅ ፡ ሕጎች ፡ ሊሆኑ ፡ ይቅርና ፡ እንዲያውም ፡ ሕግ ፡ በሚወስነው ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ነጻነትን ፡ ይሰጣሉ ፡ (እንደዚሁም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ነጻነትን ፡ የሚሰጡ ፡ የውል ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚ ነት ፡ የሚያገኙት ፡ የተዋዋይ ፡ ወገኖችን ፡ ነጻነት ፡ የሚወስኑ ፡ አስገዳጅ ፡ ድንጋጌ ዎች ፡ በወሰኑት ፡ ክልል ፡ ብቻ ፡ ነው) ። ከጥንታዊው ፡ ጋብቻን ፡ ድርጅት ፡ ከሚያ ደርገው ፡ የሌሎች ፡ አገሮች ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ በጣም ፡ የተለየው ፡ በ“መግቢያው” ውስጥ ፡ የተሰጠው ፡ ከሁሉ ፡ የተሻለ ፡ ምሳሌ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯፳፪ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ቁጥር ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ በጋብቻቸው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ለግላዊ ፡ ግንኙ ነታቸው ፡ መብትና ፡ ግዴታዎቻቸውን ፡ እንዲስማሙባቸው ፡ ይፈቅድላቸዋል ። የዚህ ፡ ድርሰት ፡ ጸሐፊ ፡ ይህን ፡ የባልና ፡ የሚስቱን ፡ መብት ፡ የሚወስነው ፡ ቁ ጥር ፡ ፲፯፴፩ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ማለቱ ፤ ሕጉ ፡ መጀመሪያ ፡ ሲነበብ ፡ ጉልህ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮችን ፡ አሳጥሮ ፡ ለመናገር ፡ ያህል ፡ ነበር ። ቍጥር ፡ ፲፯፴፫ ፡ ፲፯፴፬ ፡ እና ፡ ፲፯፴ ፡ (ሕጉ ፡ በጋብቻ ፡ ውል ፡ ሊሻሻሉ ፡ አይችሉም ፡ ብሎ ፡ የሚወስናቸው ፡ ቍጥሮች) ፡ በቍጥር ፡ ፲፯፴፩ ፡ የተጠቀሱትን ፡ የመከባበር ፡ የመደጋገፍና ፡ የመረ ዳዳት ፡ ግዴታዎችን ፡ በዝርዝር ፡ ከመግለጻቸው ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ሞያ ፡ የላቸውም። እነዚህ ፡ ገደቦች ፡ ግን ፡ በቍጥር ፡ ፲፯፳፪ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ ያለውን ፡ ልዩ ፡ የውል ፡ ስሜት ፡ አያስቀሩትም ፤ ይህ ፡ ስሜት ፡ ጋብቻ ፡ ቀዋሚ ፡ ድርጅት ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ጽንስ ፡ ሐሣብ ፡ በተስፋፋባቸው ፡ የሕግ ፡ አቋሞች ፡ አይገኝም ።[15] እዚ ሁ ፡ ላይ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ክሽችኖቪች ፡ የሚከራከሩት ፡ በመጻሕፍት ፡ ሕግና ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ነው ። ቅር ፡ የሚያሰኘው ፡ ግን ፡ ከነዚህ ፡ ምንጮች ፡ ማን

---

14. እንዲህ ፡ ያለው ፡ መብት ፡ በገንዘብ ፡ እንደማይሸጥና ፡ እንደማይለወጥ ፡ የሚቆጥረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፱ ፡ ይህንን ፡ ሐሣብ ፡ ይደግፋል ።

15. በዚህ ፡ ሐሣብ ፡ መሠረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ጋብቻ ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ በራሳቸው ፡ ስምም ነት ፡ ሊያደርጉ ፡ የሚችሉት ፡ ጋብቻውን ፡ ለመፈጸም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ስምም ነት ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ወዲያውኑ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ ፍጹም ፡ ይገዛሉ ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። ይህ ፡ ሐሣብ ፡ የታማኝነትን ፡ ተግባር ፡ በአስገዳጅነት ፡ ከተደነገገባቸው ፡ ነገሮች ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ በማይቆጥረው ፡ እንደ ፡ ቍ. ፲፯፭፫ ፡ በመሰለ ፡ ድንጋጌ ፡ ይደገፋል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግን ፡ የሥራ ፡ ክፍኞቹ ፡ መጥቀሳቸው ፡ የሚያከራክር ፡ ነው ። አመል ካች ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ አመንዝራው ፡ ተግባር ፡ ፈቃዱን ፡ ከገለጸ ፡ ክስ ፡ ሊኖር ፡ እንደማ ይችል ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ይወስናል ። ስለዚህ ፡ ከባልና ፡ ከሚስት ፡ አንዱ ፡ አመንዝራ ፡ ተግባር ፡ እንዲፈጽም ፡ በጋብቻቸው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖር ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ምንም ፡ ምክንያት ፡ አይኖረውም ፤ ምክ ንያቱም ፡ ተግባሩ ፡ እንዲፈጸም ፡ ፈቃዱን ፡ በመስጠቱ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የቍ. ፲፯፱፫ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ የፈለጉትን ፡ እንዲያደርጉ ፡ ፈቃድ ፡ የሚሰጡ ፡ ብቻ ፡ መሆናቸው ፡ ምንም ፡ ሊያጠራጥር ፡ አይችልም ።

ኛውንም ፣ አለመጥቀሳቸው ፣ ነው ። የዚህ ፣ ድርሰት ፣ ጸሐፊ ፣ ግን ፣ ለክርክሩ ፣ ድጋፍ ፣ ለማግኘት ፣ የተመለከተው ፣ የፍትሐ ፣ ብሔርን ፣ ሕግ ፣ ብቻ ፣ ነው ።

የልማድን ፣ ሕግ ፣ የማይመለከት ፣ ሌላ ፣ አከራካሪ ፣ ነገር ፣ ለቤተ ፣ ዘመድ ፣ ዳኞች ፣ የተሰጠው ፣ ይዞታ ፣ ነው ። በዚህ ፣ አርዕስት ፣ ላይ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔርን ፣ ሕግ ፣ ብቻ ፣ አንብቡ ፣ ብለው ፣ ፕሮፌሰር ፣ ክሽችኖቢች ፣ ለአንባቢዎች ፣ የሰጡትን ፣ ምክር ፣ ደራሲው ፣ ተቀብሎታል ። ግን ፣ ከቤተ ፣ ዘመድ ፣ ዳኞች ፣ በቀር ፣ የፍችን ፣ ነገር ፣ ለመወሰን ፣ የሚችሉ ፣ ሌሎች ፣ ባለሥልጣኖች ፣ መኖራቸውን ፣ የሚናገር ፣ ሕግ ፣ የትም ፣ አላገኘሁም ፤ የሥራ ፣ ጓደኞቼ ፣ የጠቀሱት ፣ ቍጥር ፣ ፲፱፻፷፯ ፣ በቍጥር ፣ ፲፱፻፷፱ ፣ እና ፣ በተከታታዮቹ ፣ ቍጥሮች ፣ መሠረት ፣ የቤተ ፣ ዘመድ ፣ ዳኞች ፣ ውሳኔ ፣ የሰጡባቸውን ፣ ሁኔታዎች ፣ ያመለክታል ። እንዲህ ፣ ያሉ ፣ ውሳኔዎች ፣ ጉዳዩ ፣ በሚመለከታቸው ፣ ወገኖች ፣ በፍርድ ፣ ቤት ፣ ሕጋዊነታቸው ፣ የሚጠየቀው ፣ በቍጥር ፣ ፲፱፻፷፯ ፣ ውስጥ ፣ ባሉት ፣ ባንዳንድ ፣ በተወሰኑ ፣ ምክንያቶች ፣ ነው ። ነገር ፣ ግን ፣ ይህ ፣ ድንጋጌ ፣ ፍችን ፣ ለመወሰን ፣ በቀደምትነት ፣ ለቤተ ፣ ዘመድ ፣ ዳኞች ፣ ብቻ ፣ የተሰጠውን ፣ ሥልጣን ፣ በምንም ፣ ስሜት ፣ አይለውጠውም ።

የልማድ ፣ በሥራ ፣ ላይ ፣ መዋል ፣ ልማድን ፣ ለማጥናት ፣ ምክንያት ፣ ይሆናል ፣ በማለት ፣ የገለጽኩትንም ፣ አስተያየት ፣ ፕሮፌሰር ፣ ክሽችኖቪች ፣ ተቃውመውታል ።[16] ነገር ፣ ግን ፣ የዚህ ፣ ጽሑፍ ፣ ደራሲ ፣ በሕግ ፣ አዋቂዎች ፣ ዘንድ ፣ ስለልማድ ፣ የሚጠናበት ፣ ምክንያት ፣ ይህ ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ ያምናል ። ልማድ ፣ በሕግ ፣ ረገድ ፣ ጠቃሚነት ፣ ከሌለው ፣ ስለ ፣ ሰብአዊ ፣ ፍጡር ፣ ለሚመራመሩ ፣ ሰዎች ፣ ሊተው ፣ ይቻላል ። በሕግ ፣ አዋቂዎች ፣ ዘንድ ፣ ልማድ ፣ መጠናት ፣ ያለበት ፣ (በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ውስጥ ፣ ተዋህዶ ፣ ቢገኝም ፣ ባይገኝም) ፣ ሕግ ፣ ሁኖ ፣ እስከተሠራበት ፣ ጊዜ ፣ ድረስ ፣ ብቻ ፣ ነው ። የዚህ ፣ ነገር ፣ እውነተኛነት ፣ በኢትዮጵያም ፣ ሆነ ፣ በሌሎች ፣ ሀገሮች ፣ አንድ ፣ ነው ።

ፕሮፌሰር ፣ ክሽችኖቪች ፣ በሕገ ፣ መንግሥት ፣ አንቀጽ ፣ ፻፲ ፣ ውስጥ ፣ "ሕግ" ለሚለው ፣ ቃል ፣ ስለሚሰጠው ፣ ትርጉም ፣ ክርክር ፣ አቅርበዋል ።[17] አንባቢው ፣ መለስ ፣ ብሎ ፣ "መግቢያውን" ፣ እንደገና ፣ ቢመለከት ፣ ከፍርድ ፣ ቤት ፣ የመነጨ ፣ ሕግ ፣ ሥርዓትን ፣ የማይከተል ፣ እንደሆነና ፣ "በኢትዮጵያ ፣ በአዋጅ ፣ ለወጣ ፣ ሕግ ፣ ብልጫ" ፣ የሚሰጠው ፣ (አዋጁን ፣ የሚያወጣው ፣ ምክር ፣ ቤት ፣ የሕዝቡን ፣ የወል ፣ ፈቃድ ፣ የያዘ ፣ የሕዝቡ ፣ እንደራሴ ፣ በመሆኑ) ፣ መሆኑን ፣ ተገልጾ ፣ ያገኘዋል ።[18] እነዚህኑ ፣ ነገሮች ፣ የሥራ ፣ ክደኞቼ ፣ በልዩ ፣ አነጋገር ፣ ገልጸዋቸዋል ፤ መመለስ ፣ የሚገባው ፣ ጥያቄ ፣ ዳኞች ፣ በአዋጅ ፣ ከወጣ ፣ ሕግ ፣ በስተቀር ፣ በሌላ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ እንዲፈርዱ ፣ ይገደዱ ፣ ወይም ፣ አይገደዱ ፣ እንደሆነ ፣ ነው ። በአዋጅ ፣ ከወጣው ፣ ሕግ ፣ ጋር ፣ በሚጋጭ ፣ ነገር ፣ መሠረት ፣ እንዲፈርዱ ፣ እንደማይገደዱ ፣ ግልጽ ፣ ነው ፤ ቢሆንም ፣ የእጋጊውን ፣ የበላይ ፣ ፈቃድ ፣ (ምኞት) የማያፈርሱ ፣ ከሆነ ፣ በልማድ ፣ ከዚህ ፣ ቀደም ፣ በተሰጡ ፣ ፍርዶች ፣ እንዲያውም ፣

16. በትችቱ ፣ ውስጥ ፣ በገጽ ፣ ፲፻፲፩ ፣ ተመልከት ።
17. ከዚህ ፣ በላይ ፣ በተጠቀሰው ፣ በገጽ ፣ ፲፻፲፯ ፣ ተመልከት ። ከዚያ ፣ በኋላ ፣ የክርክራቸውን ፣ ውጤት ፣ በመጨረሻ ፣ የግርጌ ፣ ማስረጃቸው ፣ (ባ፶፯ኛው) ፣ ላይ ፣ ሊሽሩት ፣ ምንም ፣ ያህል ፣ አይቀራቸውም ። በዚያው ፣ የግርጌ ፣ ማስረጃ ፣ ላይ ፣ የሕጉ ፣ መሠረታዊ ፣ ዓላማ ፣ ፍጹም ፣ ልዩ ፣ ነው ፣ ይላሉ ። የተጠቀሰው ፣ የግርጌ ፣ ማስረጃ ፣ በሚሰጣቸው ፣ ዋና ፣ ዋና ፣ ሐሣቦች ፣ በርግጥ ፣ እንስማማለን ። ይሁን ፣ እንጂ ፣ ዳኞች ፣ "በሕጉ ፣ መሠረት" ፣ መፍረድ ፣ አለባቸው ፣ የሚለው ፣ ሐሣብ ፣ በገለጸበት ፣ በሕገ ፣ መንግሥቱ ፣ በአንቀጽ ፣ ፻፲ ፣ በመጀመሪያው ፣ ዓረፍተ ፣ ነገር ፣ ላይ ፣ በሁለታችን ፣ መሐከል ፣ ያለው ፣ ክርክር ፣ ፍጻሜ ፣ አያገኝም ።
18. መግቢያውን ፣ በገጽ ፣ ፻፶፪ ፣ ተመልከት ።

በሕግ ፡ (ሲያንስ) ፡ ትችት ፡ መሠረት ፡ እንኳ ፡ ለመፍረድ ፡ ይችሉ ፡ ይሆናል ። ዳኞች ፡ ቀድሞ ፡ የተሰጡ ፡ ፍርዶችን ፡ እንዲከተሉ ፡ የሚያስገድድ ፡ ደንብ ፡ ገና ፡ አለመቋቋሙ ፡ የሕግ ፡ ምንጭ ፡ መሆን ፡ የሚገባው ፡ በአዋጅ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አጥጋቢ ፡ ክርክር ፡ አይደለም ። ይልቁንም ፡ ምንም ፡ ሳይሳካ ፡ ቢቀር ፡ ይህንን ፡ ደንብ ፡ ለማቋቋም ፡ የተደረገው ፡ ሙከራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አጋጊ ፡ ቀድሞ ፡ የተሰጡ ፡ ፍርዶችን ፡ በአንቀጽ ፡ ፻፲ ፡ ውስጥ ፡ "ሕግ" ፡ ከሚለው ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ ልዩ ፡ አድርጎ ፡ እንዳልቆጠራቸው ፡ ያመለክታል ።

በመጨረሻ ፡ በሥራ ፡ ጓደኛዬ ፡ ሐተታ ፡ ላይ ፡ ሊሰጡ ፡ ስለሚችሉት ፡ ሐሣቦች ፡ የቀረቡትን ፡ ምሳሌዎች ፡ ከመጨረሴ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ እስላም ፡ ሕግ ፡ ለማየት ፡ እፈልጋለሁ ። ሌላ ፡ ሃይማኖት ፡ ለመከተል ፡ ነጻነት ፡ ላላቸው ፡ "ልዩ ፡ ሕግ" ይኖራቸው ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ፡ ብዬ ፡ ከቶ ፡ አልተከራከርኩም ።[19] እዚህ ፡ ሀገር ፡ የእስላም ፡ ሕግ ፡ አሁንም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላል ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ይህንን ፡ ሐሣብ ፡ ማብራራት ፡ አስፈላጊ ፡ አልመሰለኝም ፡ ነበር ፤ ምክንያቱም ፡ አሁንም ፡ ከሚሠራባቸው ፡ የእስላም ፡ ሕጎች ፡ አብዛኞዎቹ ፡ ከሕጋዊ ፡ ልማድ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ እንደሚቆጠሩና ፡ ይህም ፡ ባይሆን ፡ የእስላም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መኖር ፡ የእስላም ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለመዋሉ ፡ በቂ ፡ መረጃ ፡ እንደሆነ ፡ ግልጽ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ይህም ፡ እንደ ፡ ጊዜያዊ ፡ መፍትሔ ፡ የተቆጠረ ፡ ይመስላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የ"መግቢያው" ፡ ዓላማ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ ያሁኑን ፡ ሁኔታቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፡ የእስላምን ፡ ሕግ ፡ ቸል ፡ ለማለት ፡ አልቻልኩም ። የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ሕግ ፡ የሚያብራሩ ፡ መጻሕፍት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆናቸው ፡ ፍጹም ፡ ግልጽ ፡ ነው ። የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲም ፡ ወደዚሁ ፡ ጉዳና ፡ ለማምራት ፡ አበረታች ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ አልጠበቀም ።[20]

## የሕጉ ፡ ሰዓት ።

ፕሮፌሰር ፡ ክሽችኖቪች ፡ በድርሰታቸው ፡ በመጨረሻዎቹ ፡ መስመሮች ፡ ላይ ፡ የሕጉን ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ በመመለስ ፡ ስላለው ፡ ችግር ፡ አውስተዋል ። ከሰጣቸው ፡ ትችቶች ፡ (ዋናዎቹን ፡ ተነጋግረንባቸዋል) ፡ ልንረዳ ፡ እንደምንችለው ፡ የዚህ ፡ ድርሰት ፡ ጸሐፊ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ዕድገት ፡ እንቅፋት ፡ እንደሆነ ፡ የሚያስመስል ፡ አስተያየት ፡ ገልጸዋል ። እኔ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ ይህ ፡ የሚያሳየው ፡ ፕሮፌሰሩ ፡ ድርሰቴንና ፡ በተለይም ፡ ለመራቀቅ ፡ ብቻ ፡ የሚጠቅሙትን ፡ ሕጋዊ ፡ አተረጓጎሞች ፡ ከሚገባቸው ፡ በላይ ፡ ማጋነናቸው ፡ ነው ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ልማድ ፡ አገሩ ፡ ውስጥ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉ ፡ አያጠራጥርም ። (ፕሮፌሰር ፡ ክሽችኖቪች ፡ ወደዚህ ፡ የሐሣብ ፡ መደምደሚያ ፡ የሚያደርስ ፡ በር ፡ በርግጥ ፡ ከፍተዋል) ። የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ ዕድገት ፡ የሚያሰናክለው ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ በሙሉ ፡ ያለንን ፡ ዕውቀት ፡ ማዳበራችን ፡ አይደለም ። ይህ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ዛሬ ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ለሚካሄደው ፡ የጥናትና ፡ የምርምር ፡ ድርጅቶች ፡ መስፋፋት ፡ ምንም ፡ ምክንያት ፡ ባልተገኘለትም ፡ ነበር ።

ክጃክስ ፡ ቫንደርሊንደን ፡
በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡
የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ።

19. ትችቱን ፡ ገጽ ፡ ፲፻፲፩ ፡ ተመልከት ።
20. ደራሲው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስላለው ፡ ስለ ፡ ሰዎችና ፡ ስለ ፡ ቤተ ዘመድ ፡ ሕግ ፡ ጽሑፍ ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ነው ።